የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አራተኛ ዓመት ቁጥር ፳፩
አዲስ አበባ–የካቲት ፲፫ ቀን ፲፱፻፺

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

4th Year No. 21
ADDIS ABABA - 20th Feb., 1998

ማውጫ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፴/፲፱፻፺ ዓ.ም.
የውሽውሽ ሻይ ልማት ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........................................ ገጽ ፮፻፹፱

CONTENTS

Council of Ministers of Regulations No. 30/1998
Wush Wush Tea Development Enterprise Establishment Council of Ministers Regulations ... Page 689

### የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፴/፲፱፻፺

### የውሽውሽ ሻይ ልማት ድርጅትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፯ አንቀጽ ፭ እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፵፯/፩/ /ሀ/ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል ፡፡

፩· አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የውሽውሽ ሻይ ልማት ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፴/፲፱፻፺" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪· መቋቋም

፩· የውሽውሽ ሻይ ልማት ድርጅት (ከዚህ በኋላ "ድርጅቱ" እየተባለ የሚጠራ) የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል ፡፡

### COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS No. 30/1998

### COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE WUSH WUSH TEA DEVELOPMENT ENTERPRISE

These Regulations are issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 4/1995 and Article 47 (1) (a) of the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

1. Short Title

These Regulations may be cited as the "Wush Wush Tea Development Enterprise Establishment Council of Ministers Regulations No. 30/1998."

2. *Establishment*

1) There is hereby established the Wush Wush Tea Development Enterprise (hereinafter 'the Enterprise') as a public enterprise.

ያንዱ ዋጋ 2.30
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፪· ድርጅቱ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ መሠረት ይተዳደራል ።

፫· <u>ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን</u>

በመንግሥት የሚሰየም አካል የድርጅቱ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል ።

፬· <u>ዋና መሥሪያ ቤት</u>

የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት በውሽውሽ ይሆናል ። እንደአስፈላጊነቱም በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል ።

፭· <u>ዓላማ</u>

ድርጅቱ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው ፡

፩· የሻይ ተክል ልማት ማካሄድ ፤

፪· የሻይ ቅጠልን በመጀመሪያ ደረጃ ማዘጋጀት ፤

፫· ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ተዛማጅ ሥራዎችን ማካሄድ ።

፮· <u>ካፒታል</u>

ለድርጅቱ የተፈቀደው ካፒታል ብር ፵፩ ሚሊዮን ፭፻፮ ሺህ (አርባ አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ስድስት ሺህ ብር) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር ፳ ሚሊዮን ፯፻፶፪ ሺህ ፭፻፹፮ (ሃያ ሚሊዮን ሰባት መቶ ሃምሳ ሁለት ሺህ አምስት መቶ ሰማንያ ስድስት ብር) በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል ።

፯· <u>ኃላፊነት</u>

ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም ።

፰· <u>ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ</u>

ድርጅቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል ።

፱· <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ የካቲት ፲፫ ቀን ፲፱፻፺ ዓ·ም

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ሚኒስትር

2) The Enterprise shall be governed by the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

3. *Supervising Authority*

A body to be designated by the Government shall be the supervising authority of the Enterprise.

4. Head Office

The Enterprise shall have its head office in Wush Wush and may have branch offices elsewhere, as may be necessary.

5. *Purposes*

The purposes for which the Enterprise is established are:

1) to engage in the development of tea plantation;

2) to engage in the preliminary processing of tea;

3) to engage in any other related activities conducive to the attainment of its purposes.

6. *Capital*

The authorized Capital of the Enterprise is Birr 41,506,000 (forty one million five hundred six thousand Birr) of which Birr 20,752,586 (twenty million seven hundred fifty two thousand five hundred eighty six Birr) is paid up in cash and in kind.

7. *Liability*

The Enterprise shall not be held liable byond its total assets.

8. *Duration*

The Enterprise is established for an indefinite duration.

9. *Effective Date*

These Regulations shall enter into force on the date of their publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 20th day of February, 1998.

MELES ZENAWI

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE